**የባህሪ ደንቦች**
**የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የህዝብ ቤተ-መፃህፍት**

---

19 DCMR § 810
D.C. Mun. Regs. Tit. 19, § 810

810. የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የህዝብ ቤተ-መፃህፍት አጠቃቀምን የሚያስተዳድሩ የባህሪ ደንቦች

**810.1 መግቢያ**

የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የህዝብ ቤተ-መፃህፍት (DCPL) የባህሪ ደንቦች ሦስት ዋና ዓላማዎች አሉት፥ (1) የሁሉም የቤተ-መፃህፍት ደንበኞችን መብቶች እና ደህንነትን ለመጠበቅ፣(2) እና የሰራተኛ አባላት መብቶች እና ደህንነትን ለመጠበቅ እና (3) የቤተ-መፃህፍቱን ቁሳቁሶች፣ መገልገያዎች እና ንብረት ለመጠበቅ

DCPLየ ሁሉም ደንበኞች ያለ አድሎ፣ ማስፈራሪያ፣ የጉዳት ስጋት ወይም የግላዊነት ወረራ መረጃን በነፃ እና በእኩልነት የማግኘት እና ቤተ-መፃህፍቱን የመጠቀም መብትን ይደግፋል። DCPL ለሁሉም ደንበኞች ወዳጃዊ፣ ጨዋ እና አክባሪ አገልግሎት እንዲሁም አስደሳች፣ ንፁህ እና ምቹ አከባቢ ለማቅረብ ወስኗል።

የቤተ-መፃህፍቱ ቁሳቁሶችን እና መሳሪያ ያለፍቃድ ማዉጣትን ለመከላከል እና የቤተ-መፃህፍቱ ሰራተኛ እና ደንበኞች ጤና እና ደህንነት ሲባል፣DCPL የደንበኛ ይዞታዎች፣ ቦርሳዎች፣ የጀርባ ሻንጣዎች፣ ሻንጣዎች፣እሽጎች፣ የግዢ ሻንጣዎች፣ የስራ ሻንጣዎች እና ሌሎች ቁሳቁሶችን ጨምሮ የመመርመር መብት ይይዛል።

በአስቸኳይ አዋጅ ጊዜ ወይም በከንቲባው የታወጀ የህዝብ ጤና ድንገተኛ ጊዜ አዋጅ ወይም የሰራተኞችን ወይም የህዝቡን ጤና፣ ደህንነት እና ሰላም መጠበቅ አስፈላጊ ሲሆን፣ የቤተ-መፃህፍት የባለ አደራዎች ቦርድ መመሪያዎችን፣ ደንቦችን፣ ፖሊሲዎችን እና ሂደቶችን እንዲያሻሽል ለዋና ዳይሬክተር ስልጣን ይሰጣል።

**810.2 ትርጓሜዎች እና ወሰን**

እነዚህ የባህሪ ደንቦች በDCPL የምቆጣጠሩ እና የሚሰሩ ሁሉም ህንፃዎች እና ሁሉም መሬቶች (ህንፃዎች እና መሬቶቻቸው እንዲሁም "ግቢዎች" ተብለው ይታወቃሉ) እና ወደ ግቢው የሚገቡ ሁሉም ደንበኞች ላይ ተግባራዊ ይሆናል። ከታች የተዘረዘሩት የቤተ-መፃህፍቱ የባህሪ ደንቦች ናቸው። እነዚህን ደንቦች የሚጥሱ ደንበኞች ከግቢው እንዲወጡ ሊደረጉ ይችላሉ እና በD.C. የህዝብ ቤተ-መፃህፍት ስልጣን፣ ከታች ለተዘረዘሩት የጊዜ ቆይታ፣ከሁሉም የቤተ-መፃህፍቱ ግቢዎች ይገለላሉ።

**810.3 ማስፈጸሚያ**

የቤተ-መፃህፍት ሰራተኛ፣ የቤተ-መፃህፍ ፖሊስ፣ እና/ወይም የሜትሮፖሊታን ፖሊስ መምሪያ (MPD) መኮንኖች የተከለከሉ ድርጊቶችን እና ባህሪያትን ለማቆም ጣልቃ ሊገቡ ይችላሉ። ህግን መስበር ለህግ ስር መዋል እና ክስ ሊያደርግ ይችላል። እነዚህን ደንቦች አለመከተል ከአንድ ቀን እስከ አምስት ዓመታት ለሚቆይ ጊዜ ከቤተ-መፃህፍት ንብረት የሚያግድ ማስታወቂያ ማዉጣትን ሊያስከትል ይችላል። የዕገዳ ማስታወቂያ ከወጣ፣ ሁሉም የDCPL መገኛ ቦታዎች ላይ ይተገበራል እና የDCPL መብቶች ማገድን ጨምሮ፣ የDCPL ኮምፒዉተር እና ሌላ መሳሪያን መጠቀምን ጨምሮ፣ ግን በሱ ብቻ ሳይወሰን። ከታገዱ፣ደንበኞች በD.C. የህዝብ ቤተ-መፃህፍት ሰራተኛ ፎቶግራፋቸው ወይም ቪዲዮቻቸው ሊያዝ ይችላል ዕገዳዉን ለማስፈጸም።

**810.4 የዕገዳ ማስታወቂያዎች አስተዳደራዊ ግምገማ**

(a) ዕገዳዉ ከሰባት (7) ቀናት በላይ ከሆነ፣ የዕገዳ ማስታወቂያን የሚቀበል ግለሰብ አስተዳደራዊ ግምገማን ሊጠይቅ ይችላል። ይህ ጥያቄ ከዕገዳ ማስታወቂያ ቀን አስር (10) የስራ ቀናት ዉስጥ ተደርጎ በጽሁፍ መግባት አለበት ወደ፥

የህዝብ ደህንነት ዳይሬክተር
Martin Luther King Jr. የመታሰቢያ ቤተ-መፃህፍት
901 G Street NW
Washington, DC 20001

(b) ዋና ዳይሬክተሩ ወይም ተወካይ በሠላሳ (30) የካሌንደር ቀናት ዉስጥ የእገዳው አስተዳደራዊ ግምገማ የመጨረሻ ዉሳኔን ያሳልፋል። እገዳው የተጣለበት ግለሰብ የመጨረሻ ዉሳኔን ከመጨረሻ ዉሳኔ ማስታወቂያ ቀን በሠላሳ (30) ቀናት ወስጥ ለኮሎምቢያ ዲስትሪክት የበላይ ፍርድ ቤት የሲቪል ክፍል አቤቱታ ማቅረብ ይችላል።

በቤተ-መፃህፍቱ የባለአደራ ቦርድ ጸድቋል
ሀምሌ 22, 2020

### 810.5 ምክንያታዊ ማረፊያ

በአካል ጉዳተኝነት ወይም የጤና ችግር ምክንያት፣ የዚህ መመሪያዎች ምክንያታዊ ማሻሻያ ለመጠየቅ የሚሹ የቤተ-መፃህፍቱ ደንበኞች የቤተ-መፃህፍቱ ሰራተኛን ማግኘት ወይም ለADA አስተባባሪ በ 202-727-1101መደወል ይችላሉ።

### 810.6 የባህሪ ደንቦች

ለህዝቡ እና ለሠራተኛ ደህንነት እና ምቹነት፣ እና ለቤተ-መፃህፍት አሰራሮች ምቹ የሆነ አካባቢን ለመፍጠር፣ ቀጥሎ ያሉ ደንቦች እና ውጤቶች ተግባራዊ ይሆናሉ። እነዚህ ድርጊቶች የቤተ-መፃህፍቱ ህንፃዎች ላይ የተከለከሉ ናቸው፥

(a) <u>ምድብ አንድ ደንቦች እና ውጤቶች፥</u> የትኛዉም ደንበኛ፣ ዕድሜው ዘጠኝ (9) እና የሚበልጥ፣የቤተ-መፃህፍቱ ህንፃዎች ላይ እያለ የምድብ አንድ ደንቦችን የጣሰ፣ ችግሩ እስከሚስተካከል ድረስ ከህንፃዎቹ ይከለከላል። በዛው ደንበኛ ቀጣይ ጥፋቶች የሰዉየውን አስቸኳይ መዉጣት እና ከሁሉም የDCPL ህንፃዎች መከልከልን ያስከትላል፣እንደሚቀጥለው፥

| ዕድሜ | መጀመሪያ | 2ኛ ጥሰት (30 ቀናት ዉስጥ) | 3ኛ ጥሰት (30 ቀናት ዉስጥ) | 4ኛ ጊዜ (30 ቀናት ዉስጥ) |
|---|---|---|---|---|
| 9+ | ችግር እስከሚስተካከል ድረስ ቤተ-መፃህፍት ይልቀቁ | 1 ሳምንት | 1 ወር | 3 ወራት |
| 0-8 | ለእንክብካቤ ሰጪ ማስጠንቀቂያ እና ሪፈራል | | | |

(1) በባዶ እግር ወይም ባዶ ደረት የDCPL ህንፃዎች ላይ መሆን፤ ሸሚዞች እና ካልሲዎች ሁሉ ጊዜ ያስፈልጋሉ።

(2) የየትኛዉም የሚቆጣጠር ዕጽ ወይም የሚያሰክር መጠጥ የሚታወቅ ተጽኖ ስር መሆን።

(3) 9″L x 14″W x 22″H የሚበልጡ ቦርሳዎችን ይዞ መምጣት። ደንበኞች በአንድ ሰው ሁለት ቦርሳዎችን ይዞ መምጣት ይፈቀድላቸዋል፣ ግን እያንዳንዱ ቦርሳ ከ9″L x 14″W x 22″H የሚያንስ መሆን አለበት። ቁሳቁሶች በቀላሉ ከላይ የተገለጹ ስፍረቶች ያለው የመስፈሪያ ሳጥን ዉስጥ መግባት አለባቸው። የተወረሩ የግል ቁሳቁሶችም የተከለከሉ ናቸው። ደንበኛው የግል ዝግጅትን እየተሳተፈ ከሆነ፣ ቦርሳ(ዎች) የመጠን የገደቦችን ሊያልፍ ይችላል ምክንያቱም አዘጋጅ(ጆች) የኮት እና የቦርሳ ማመልከት አገልግሎትን እንደሚያቀርብ ስለሚጠበቅ።

(4) በየትኛዉም ምክንያታዊ ሰው ከስድስት (6) ዕርምጃ ርቀት የሚሸተት እና/ወይም ሌሎች የቤተ-መፃህፍት ተጠቃሚዎችን የሚረብሽ ሽታ ያለው ደንበኛ።

(5) በሽታ፣ ቆሻሻ ወይም መፍሰስ ምክንያት ብጥብጥ የሚፈጥር ወይም የቤተ-መፃህፍት ተጠቃሚዎችን የሚረብሽ ምግብ ወይም መጠጥ መዉሰድ። የታሸጉ ዕቃዎች ዉስጥ ያሉ አልኮል የሌላቸው መጠጦች እና ምግብ የተሰየሙ አካባቢዎች ብቻ ይፈቀዳሉ።

(6) መሬት ላይ መተኛት፣መተኛት፣ ወይም ህንፃዎች ላይ የዕንቅልፍ አዝማሚያ። የሚቀመጡ ደንበኞች በቤተ-መፃህፍት የቀረቡ መቀመጫን መጠቀም አለባቸው (ወንበር፣ ሰፋ፣ ወዘተ.)። ደንበኞች በቤተ-መፃህፍት ሰራተኛ አባል ካልጸደቀ በስተቀር ወለል፣ የእግር መንገድ፣ወዘተ ላይ መቀመጥ የለባቸዉም እና መተላለፊያዎች፣ መዉጫዎች፣ መንገዶች፣ ወይም መግቢያዎች መዝጋት የለባቸዉም።

(7) የግል ኤሌክትሮኒክስን ያለ ሄድ ፎን ወይም ሌሎችን በሚረብሽ የድምፅ መጠን መጠቀም

(b) <u>ምድብ ሁለት ደንቦች እና ውጤቶች፥</u> የቤተ-መፃህፍት ህንፃዎች ላይ እያለ የምድብ ሁለት ደንቦችን የሚጥስ ደንበኛ ለስድስት (6) ወራት የደንበኛው መዝገብ ላይ የሚቆይ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል። በዛው ደንበኛ በስድስት (6) ወራት የጊዜ ገደብ ዉስጥ የሚፈጸሙ ቀጣይ ጥፋቶች የሰውየውን አስቸኳይ ማዉጣት እና ከሁሉም የD.C. የህዝብ ቤተ-መፃህፍት ህንፃዎች መታገድን ያስከትላሉ። እንደሚከተለው፥

| ዕድሜ | መጀመሪያ | 2ኛ ጥሰት (6 ወራት ዉስጥ) | 3ኛ ጥሰት (6 ወራት ዉስጥ) | 4ኛ ጥሰት (6 ወራት ዉስጥ) |
|---|---|---|---|---|
| 18+ | ማስጠንቀቂያ | 3 ወራት | 6 ወራት | 1 አመት |

በቤተ-መፃህፍቱ የባለአደራ ቦርድ ጸድቋል
ሀምሌ 22, 2020

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 13-17 | ማስጠንቀቂያ | 1 ወር | 3 ወራት | 6 ወራት |
| 9-12 | ማስጠንቀቂያ | 1 ሳምንት | 2 ሳምንታት | 1 ወር |
| 0-8 | ማስጠንቀቂያ፣ ሪፈራል ለእንክብካቤ ሰጪ እና/ወይም የቤተ-መፃህፍት ፖሊስ ወይም MPD። | | | |

(1) መጠየቅ፣ አቤቱታ ማቅረብ፣ ወይም የተፃፉ ቁሳቁሶችን መበተን ወይም መሳል፣ ለፖለቲካ፣ በጎ አድራጎት ወይም ሃይማኖታዊ ዓላማዎች ህንፃዎች ላይ ማድረግ።

(2) የቤተ-መፃህፍት አገልግሎቶችን ለመጠቀም፣የህዝብ ኮምፒዉተርን መጠቀም ጨምሮ፣ የሌላ ሰዉን የቤተ-መፃህፍት ካርድ መጠቀም የተከለከለ ነው። እያንዳንዱ ደንበኛ የራሳቸዉን የቤተ-መፃህፍት ካርድ መጠቀም አለባቸው እና እነዚህ ካርዶች የማይተላለፉ ናቸው፣የቤተ-መፃህፍት ካርድዎን ለሌላ ሰው መዋስ የተከለከለ ነው። ይህንን ደንብ መጣስ ዉስጥ ጥቅም ላይ የዋለ የቤተ-መፃህፍት ካርዶች ከማስጠንቀቂያ በኋላ ይታገዳሉ።

(3) ቁሳቁሶችን ወይም የግል ይዞታዎችን ህንፃዎች፣ መሳሪያ ወይም ዕቃዎች ላይ ወይም ወደሱ የቤተ-መፃህፍት ሰራተኛ ወይም የደንበኛ የቤተ-መፃህፍት አጠቃቀም ጋር ጣልቃ በሚገባ ሁኔታ ማስቀመጥ፣ ወይም የግል ይዞታዎችን ያለ ጥበቃ መተው።

(4) ብስክሌት፣ ወይም ሌላ ተመሳሳይ ዕቃዎችን የቤተ-መፃህፍት ህንፃ ላይ ማምጣት፣ የሚጨምረው፣ ግን በዚህ ብቻ ያልተወሰነ፣ አልባሳት ወይም የተሸፈኑ የበር መንገዶች። የቤተ-መፃህፍት ህንፃዎች ላይ የሚሰሩ ብስክሌቶች ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ዕቃዎች በምናለብኝነት ወይም ያለጥበቃ መተዉ።

(5) የሚሠሩ የሮሌር ስኬቲንግ፣ የስኬትቦርዶች፣ ሃቨርቦርዶች፣ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ዕቃዎችን የቤተ-መፃህፍት ህንፃዎች ላይ ወይም ዉስጥ ማስቀመጥ።

(6) የቤተ-መፃህፍት ህንፃዎች ዉስጥ እንስሳቶችን ማምጣት (ከአገልግሎት እንስሳቶች ዉጭ)፣ በቤተ-መፃህፍት የጸደቀ ዝግጅት ላይ የተፈቀደ ዉጭ፣ ወይም እንስሳትን ሳያስሩ ወይም ያለጥበቃ የቤተ-መፃህፍት ህንፃዎች ላይ መተው።

(7) የቤተ-መፃህፍት መፀዳጃ ቤቶችን፣ የገላ መታጠቢያ፣ የመላጫ፣ ፀጉር መታጠብ ጨምሮ ፣ግን በዚህ ብቻ ሳይገደቡ፣ያለአግባብ መጠቀም እና ከአንድ ሰው በላይ ሆኖ የመፀዳጃ ቤት ጋጣ ዉስጥ መሆን (ከህፃናት ወይም ዕርዳታ የሚፈልጉ አዋቂዎች ጋር ካልሆነ በስተቀር)።

(8) የተኛዉም የቤተ-መፃህፍት ህንፃዎች ላይ ወይም ዉስጥ፣በምክንያታዊነት ያልተቆጣጠሩ ወይም ያልተጠበቁ የሚመስሉ፣አንድ ወይም ብዙ ስምንት (8) ዓመት ወይም በታች የሆኑ ህፃናትን መተው።[እባክዎ ያልተጠበቁ ህፃናት ፖሊሲን ይመልከቱ]

(9) ከአስራ ሦስት(13) ዓመት ዕድሜ እና ከዛ በላይ የሆኑ ደንበኞች የህፃናት አካባቢን ከመጠቀም የተከለከሉ ናቸው፣የአስራ ሁለት (12) ዓመት ዕድሜ ወይም ከዛ በታች የሆኑ ህፃናት ጋር መሆን ወይም ከስብስብ ዕቃን መምረጥ ካልሆነ በስተቀር።

(10) ከሃያ(20) ዓመት ዕድሜ እና ከዛ በላይ የሆኑ ደንበኞች እና የአስራ ሁለት (12) ዓመት ዕድሜ ወይም ከዛ በታች የሆኑ ህፃናት የወጣቶች አካባቢን ከመጠቀም የተከለከሉ ናቸው፣ ከአስራ ሦስት (13) እስከ አስራ ዘጠኝ (19) ዕድሜ ያላቸው ወጣቶች ጋር መሆን ወይም ከስብስብ ዕቃን መምረጥ ካልሆነ በስተቀር።

(11) ከአስራ ሦስት(13) ዓመት ዕድሜ እና ከዛ በላይ የሆኑ ደንበኞች ለልጆች የተሰየመ የትኛዉም መፀዳጃ ቤትን ከመጠቀም የተከለከሉ ናቸው። የልጆች መፀዳጃ ቤቶች ለአስራ ሁለት (12) ዓመት ዕድሜ ወይም ከዛ በታች የሆኑ ልጆች፣ እና እንክብካቤ ሰጪዎቻቸው ብቸኛ መጠቀሚያ ናቸው።

(12) በትምህርት ጊዚያት የቤተ-መፃህፍት ንብረት ላይ ያሉ አስራ ስምንት(18) ዓመት ዕድሜ በታች የሆኑ ደንበኞች በቤተ-መፃህፍት ሰራተኛ ጥየቃ ከትምህርት ቤት የመቅረት ፈቃድ ማረጋገጫን ማቅረብ አለባቸው።

(13) የቤተ-መፃህፍት አጠቃቀምን የሚረብሽ ወይም ጣልቃ የሚገባ ዉጥንቅጥ፣ ቆሻሻ ወይም ፈሳሾችን መተው ወይም ዉጥንቅጥ፣ ቆሻሻ ወይም ፈሳሾችን መፍጠር።

(c) ምድብ ሦስት ደንቦች እና ውጤቶች፥ የቤተ-መፃህፍት ህንፃዎች ላይ እያለ የምድብ ሦስት ደንቦችን የሚጥስ ማንኛዉም ደንበኛ መጀመሪያ የቤተ-መፃህፍት ደንቦችን ሊያዉቅ ይገባል። በዛው ደንበኛ በአንድ ዓመት ዉስጥ የሚፈጸሙ ቀጣይ ጥፋቶች የሰውየውን አስቸኳይ ማዉጣት እና ከሁሉም የDCPL ህንፃዎች መታገድን ያስከትላሉ፣ እንደሚከተለው፥

| ዕድሜ | መጀመሪያ | 2ኛ ጥሰት (አንድ ዓመት ዉስጥ) | 3ኛ ጥሰት (አንድ ዓመት ዉስጥ) | 4ኛ ጥሰት (አንድ ዓመት ዉስጥ) |
|---|---|---|---|---|
| 18+ | 1 ወር | 3 ወራት | 1 አመት | 2 ዓመታት |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 13-17 | 1 ሳምንት | 1 ወር | 6 ወራት | 1 አመት |
| 9-12 | የቀኑ የቀረ ጊዜ | 1 ሳምንት | 1 ወር | 3 ወራት |
| 0-8 | ማስጠንቀቂያ፣ ሪፈራል ለእንክብካቤ ሰጪ እና/ወይም የቤተ-መፃህፍት ፖሊስ ወይም MPD። | | | |

(1) የተለመደ የቤተ-መፃህፍት አሰራርን የሚረብሽ ወይም ጣልቃ የሚገባ ጸባይ ዉስጥ መግባት፣ወይም የቤተ-መፃህፍት ሰራተኛ ወይም ደንበኞችን የሚረብሽ፣ የሚያካትተው ግን በዚህ በቻ ያልተወሰነ፣ተሳዳቢ ወይም የሚያስፈራራ ቋንቋ ወይም ምልክቶችን መጠቀም፣ ምክንያታዊ ያልሆነ ድምፅ የሚፈጥር ጸባይ፣ከፍ ያለ ድምፅ ወይም ጫጫታን የሚፈጥር አካላዊ ባህሪ ወይም ማውራትን የያዘው ጸባይ። ይህ የሚጨምረው ሁሉም የትንኮሳ ዓይነቶችን፣የጾታ ትንኮሳን ጨምሮ። አስፈላጊ መስለው ከታዩ አንዳንድ ጥሰቶች ወደ ምድብ አራት ሊዛወሩ ይችላሉ።

(2) የ2012 የወጣቶች መሸማቀቅ መከላከያ ህግ፣ መስከረም 14, 2012 (D.C. ህግ 19-167፤ 59 DCR 7820 (ሰኔ 29, 2012)) በተደነገገው መሰረት ሌላውን ማሸማቀቅ ዉስጥ መግባት።

(3) የትኛዉንም የቤተ-መፃህፍት ንብረት  አጥፊ፣, በዝባዥ ወይም ጉዳት በሚያደርስ ሁኔታ ያለ ስነስርዓት መጠቀም፤ወይም ራሳቸው ወይም ሌሎች ላይ የግል ጉዳት ማድረስ በሚችል ሁኔታ።

(4) ምክንያታዊ የሆነ በቤተ-መፃህፍት ሰራተኛ ወይም ህግ አስከባሪ መኮንን የሚሰጥ አቅጣጫን አለመከተል።

(5) የቤተ-መፃህፍት ዉስጥ ወይም የቤተ-መፃህፍት ንብረት ላይ፣ ማጨስ ወይም ሌላ የትምባሆ ምርት መጠቀም፣የኤሌክትሮኒክ ሲጋራዎችን ጨምሮ።

*(6) የቤተ-መፃህፍቱ ኮምፒዉተር አጠቃቀም መመሪያዎችን መጣስ።*

(7) እገዳ ላይ እያሉ የDCPL ህንፃዎችን መግባት ወይም ለመግባት መሞከር (*ማለትም፣ መተላለፍ*)። በእገዳ ጊዜ ወደ DCPL ህንፃዎች የሚመለሱ ደንበኞች ወይም ሰዎች ህጋዊ ላልሆነ መግባት ቁጥጥር ስር ዉለው ሊከሰሱ ይችላሉ በ D.C. Official Code § 22-3302 (2012 Repl.)።

(8) የትኛዉም አልኮል ያለው መጠጥን መያዝ፣ መሸጥ፣ማከፋፈል፣ ወይም መጠቀም፣ በቤተ-መፃህፍት የጸደቀ ዝግጅት ላይ የተፈቀደ ዉጭ።

(d) <u>ምድብ አራት ደንቦች እና ውጤቶች፥</u> የቤተ-መፃህፍት ህንፃዎች ላይ እያለ የምድብ አራት ደንቦችን የሚጥስ ማንኛዉም ደንበኛ በአስቸኳይ ይወጣል እና ከሁሉም የDCPL ህንፃዎች ይታገዳል፣ እንደሚከተለው፥

| **ዕድሜ** | **እያንዳንዱ ክስተት** |
|---|---|
| 18+ | 1-5 ዓመታት፣ የጉዳዩን ክብደት መሰረት፣ እና ክስተቱ አግባብ ወዳለው ህግ አስከባሪ ኤጀንሲ ሪፖርት ይደረጋል። |
| 13-17 | 3 ወር እስከ1 ዓመት፣ የጉዳዩን ክብደት መሰረት፣ እና ክስተቱ አግባብ ወዳለው ህግ አስከባሪ ኤጀንሲ ሪፖርት ይደረጋል። |
| 9-12 | 1-6 ወራት፣ የጉዳዩን ክብደት መሰረት፣ እና ክስተቱ አግባብ ወዳለው ህግ አስከባሪ ኤጀንሲ ሪፖርት ይደረጋል። |

| | |
|---|---|
| 0-8 | ማስጠንቀቂያ፣ ሪፈራል ለእንክብካቤ ሰጪ እና/ወይም የቤተ-መፃህፍት ፖሊስ ወይም MPD። |

(1) የትኛዉም የፌዴራል ወይም ኮሎምቢያ ዲስትሪክት ወንጀለኛ ደንብ፣ስርዓት፣ ኮድ፣ ወይም ህግ መጣስን የሚመሰርት የትኛዉም ድርጊትን መፈፀም፣ ወይም ለመፈፀም መሞከር።

(2) ልዩ የአካላዊ ጉዳት ማስፈራሪያን ግለሰብ፣ የግለሰቦች ቡድን፣ ወይም ንብረት ላይ መቀሰር።

(3) ወሲባዊ ጸባይ/ድርጊት ዉስጥ መግባት፣በዚህ ሳይወሰን የሚጨምረው፣ ግልፅ የሆነ የወሲባዊ መነሳሳት ወይም እርካታ ድርጊት ዉስጥ አካላዊ ማጭበርበር ወይም በልብስ በኩል የወሲብ አካልን መንካት።

---

*ምስጋናዎች*

*ምንጭ፥* በ 56 DCR 1046-1059 ጥር. 30, 2009 *ሥራ* ላይ የዋለ። የተሻሻለው *ሀ*ምሌ 26, 2013፤ *ሀ*ምሌ 31, 2017።

*ያሁኑ* በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ምዝገባ በኩል፣ ቅጽ 67፣ ቁጥር 27፣ ቀን ሰኔ 26, 2020. 19 DCMR § 810, 19 DC ADC § 810